# በኢትዮጵያ በሐይማኖት ሽፋን የሚደረግ እንቅስቃሴ መዳረሻ ወደ የት?

ቃልቤሳ ኦላና ከፊንፊኔ 3/14/12-- በኢትዮጵያ የሐይማኖትና የመንግስት ግንኙነት ታሪክ ብዙ ውጣ ውረዶችን አልፎ ዛሬ የእምነት ነፃነት፣የሃይማኖት እኩልነት እና የመንግስትና ሀይማኖት መለያየት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ በዘውዳውዊ ሥርዓት-መንግስት ሐይማኖትና መንግስት አንድ የሆኑበትና የሀገሪቷ ብሄራዊ ሐይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ሃይማኖት እንደሆነ በመደንገጉ የሌላ ሐይማኖት ተከታዮች በሐይማኖታቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ የሚቆጠሩ ብቻ ሳይሆን የእምነት ነፃነት አልነበራቸውም፡፡ በዘውዳዊው ሥርዓተ-መንግስት ህዝብና ካህናት ጳጳሳትን ቢመርጡም ንጉሰ ነገስቱ ምርጫውን ካልተቀበሉና ሹመቱን ካልፈቀዱ ጳጳሳቱ መንፈሳዊ ሥርዓት  መፈፀም እንደማይችሉ በ1948ቱ ህገ-መንግስት አንቀጽ 127 ተደንግጓል፡፡ ይህም መንግስት የኔ ነው የሚለው ሐይማኖትም ቢሆን ነፃነት ያልነበረው መሆኑን ያሣያል፡፡ በደርግ ዘመንም ሃይማኖት የአድሃሪያን መሣሪያ ጕታችና የፀረ-አብዮት መሣሪያ ነው ተብሎ ይታመን ስለበረ የሃይማኖት ተቋማት እንዲዳከሙ ተደርጓል፡፡ በደርግ ሥርዓት በእምነት የተነሣ ብዙ የሃይማኖትና የእምነት ተቋማት የተዘጉ ሲሆን ተከታዮቻቸው ለእንግልትና ለስደት ተዳርገዋል፡፡ እስከ ደርግ ውድቀት ድረስ በኢትዮጵያ ያሉ ሃይማኖቶች ለተከታዮቻቸው አገልግሎታቸውን ምሉዕ በሆነ መልኩ ማበርከት የቻሉበት ሁኔታ አልነበረም፡፡

ሁሉም የሐይማኖት ተቋማት የወል ባህሪያት አሏቸው። የሰው ልጆች በምድራዊ ህይወታቸው በሚያከናውኗቸው የተቀደሰና ሰናይ ተግባራቸው ከሞት በኋላ ከፈጣሪ ብድራታቸውን እንደሚያገኙ ያስተምራሉ፡፡ ሁሉም ሐይማኖቶች ሰላምን፣ የሰው ልጅ ክቡርነትን፣ መዋደድን፣ ሰርቶ መበልፀግን፣ መረዳዳትና መቻቻል የአስተምሮአቸው መሠረታዊያን ናቸው፡፡

እነዚህን የተቀደሱ የሐይማኖት አስተምሮዎችን የሚቃወሙ መንግስታት ዞሮ ዞሮ እየተቃወሙ ያሉት በህገራዊ ልማት፣ ሰላምና ዴሞክራሲያዊ ግንባታ በንቃት የሚሣተፍ ነፃ ማህበረሰብ መገንባትን  ስለሆነ ለመንግስትም፣ ለህዝብም  የሚበጅ አይደለም፡፡ ይህንን ታሣቢ በማድረግ የኢፌዲሪ መንግስት ከደርግ ውድቀት ማግስት ጀምሮ የሃይማኖት ጉዳይ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት መርህ ምሶሶዎች አንዱ ሆኗል፡፡ እነዚህ መርሆዎች የእምነት ነፃነት፣ የሃይማኖት እኩልነት እና የሃይማኖትና የመንግስት መለያየት (Secularism) ህገ-መንግስታዊ ዋስትና አግኝተው ባለፉት 20 ዓመታት ተግባር ላይ ውለው ውጤት እያስመዘገቡ ነው፡፡

የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት ዋና ዋና እምነቶች ተብለው የሚጠቀሱት የግለሰብና የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች መከበር፣ የፆታ እኩልነት፣ የሃይማኖትና ባህል

እኩልነት፣ ከታሪክ የተወረሰ የተዛባ ግንኙነት በማረም እና አንድ የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ መገንባት የሚሉ ናቸው፡፡ የህገ-መንግስት ዋና ዋና ዓላማዎች ደግሞ ዘላቂ ሰላምና ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ ማረጋገጥ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት እና የህግ የበላይነት የተረጋገጠበት አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ መገንባት የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህ የኢፌዲሪ መንግስት ህገ-መንግስት ዋና ዋና እምነቶችና ዓላማዎች በተግባርም ጥያቄ በማያስነሳ መልኩ ባለፉት 20 ዓመታት ተረጋግጠዋል። ሃይማኖትን በሚመለከት ዛሬ ያለውን ሁኔታ ያስተዋለ የሚነሣ ጥያቄ ከሠላማዊና ህጋዊ መንገድ ከመፈታት አልፎ ከመንግስት ጋር ለግጭት የሚጋብዝ ሁኔታ ፈፅሞ ተዘግቷል፡፡ በኢትዮጵያ ሃይማኖት የተከታዮቹ የእምነት ነፃነትና መብት ጉዳይ ሆኖ በማያሻማና ጥያቄ በማያስነሳ መልኩ ተረጋግጧል። መንግስትም ሁሉንም በእኩል ዓይን የሚያይበትና ነፃነታቸውን የሚደግፍ ስርዓት እውን አድርጓል።

በሃይማኖቶች መካከልም ለግጭት የሚጋብዝ ወይም በተመሣሣይ መልኩም በአንድ ሃይማኖት ውስጥ ግጭት የሚያስነሣ መሠረታዊ እሣቤ በህገ መንግስቱ በረተጋገጠው የእምነት ነፃነትና የሃይማኖቶች እኩልነት ከመሰረቱ ተወግዷል። ከመንግስት ጋርም ሃይማኖትን በሚመለከት ግጭት የሚጋብዝ ምንም አግባብ የለም። ሃይማኖትን በሚመለከት ከመንግስት ጋር፣ ከሃይማኖት ተቋማት ጋር እና በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ግጭት ውስጥ የሚገባና ብጥብጥ የሚፈጥር ወይም ለመፍጠር የሚከጀለው ህገ መንግስቱን ያልተቀበለና የሚቃወም ወይም ደግሞ ህገ መንግስቱን ለማፍረስ የሚከጅለው ሃይል "በሃይማኖት ሽፋም የሚንቀሳቀስ አክራሪ ሃይል" ብቻ ነው። የእምነት ነፃነት፣ የሃይማኖት እኩልነትና ሴኩላሪዝም ጉዳይ የህጎች ሁሉ የበላይ በሆነው ህገ መንግስት አዋቃሪ ምሶሶዎች አንዱና መሰረታዊ ስለሆነና ጥያቄ በማይጋብዝ ሁኔታ በተግባር ስለተረጋገጠ ነው።

የኢፌዴሪ መንግስት አጀንዳዎች ልማት፣ ዴሞክራሲና ሰላም ናቸው፡፡ እነዚህ የማይነጣጠሉ የመንግስት አጀንዳዎች በሀገሪቷ ለአንድ አፍታም እንኳ እንዲስተጓጎሉ መንግስት አይፈቅድም፡፡ መንግስት ኢትዮጵያ በማያቋርጥ ፈጣን የእድገት ለውጥ ውስጥ ገብታ የዜጐች ሁሉን አቀፍ ተጠቃሚነት ካልተረጋገጠ የሀገሪቷ እንደ ሀገር የመቀጠል ጉዳይ አጠያያቂ ነው ብሎ ያምናል፡፡ መንግስት የዜጎችን የመልማት መብት የማረጋገጥ፣ ሰላም በሰፈነበት አከባቢ የመኖር መብታቸውንና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን በተረጋጋ ሁኔታ የሚጠቀሙበት ድባብ የመፍጠርና የመጠበቅ ታላቅ ኃላፊነት አለበት። ይህ ለድርድር የሚቀርብ አጀንዳ አይደለም።

በመሆኑም መንግስት የሐይማኖት አክራሪነትን የሚመለከተው ከሃይማኖት አኳያ ሳይሆን ለሀገሪቷ ልማት፣ ሰላም እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እና ከህገ መንግስቱ አንፃር ካለው ተፅዕኖ ብቻ ነው፡፡ የሃይማኖት አክራሪነት በሃይማኖት አስተምሮ ሽፋን የተለያዩ የተቆነጣጠሩ

ሃሣቦችን በመውሰድ እና ተከታዮችን በማነሣሣት፣ የሌሎችን ሃይማኖቶችና  እምነት በማውገዝ እና አመፅ በመቀስቀስ ህገ-መንግስታዊ ግዴታዎችን ባለማክበር የሚገለፅ ትምህርትና ድርጊት ነው፡፡ ድርጊቱ በሃይማኖት ሽፋን ፖለቲካን ማራመድን የሚመለከት ስለሆነ በሃይማኖቶችና እምነት ተቋማት ውስጥ በአመራሩና በተከታዮቻቸው ሰርጎ በመግባት የፖለቲካ አጀንዳን በማራመድ ህዝቡን ለአመፅ መቀስቀስና ከዚሁ በሚገኘው ትርፍ የመንግስት ተአማኒነትን በማሣጣት የግል ወይም የቡድን የፖለቲካ ፍላጐትን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሣይሆን አመፅ በማራመድ፣በዚሁ ሂደትም የመንግስት ስልጣንን ለመያዝ ወይም ለመጋራት የሚደረግ አፍራሽ ተግባር ነው፡፡ ከዚህም አለፍ ሲል ደግም መንግስትንና ሰላማዊ ህዝብን ህገ-መንግስታዊ፣ ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ አካሄድ ሣይሆን በአመፅና ብጥብጥ መንገድ በማስገደድ የግል ፍላጐትን የግለሰብም ይሁን የቡድንን ፍላጎት በመንግስትና በህዝብ ላይ ለመጫን የሚደረግ ርብርብም ነው፡፡

የሐይማኖት አክራሪዎች መንግስትን ከሃይማኖት ገለልተኛ አድርገው ያለማቅረብ እሣቤም ከዋናው ከተነሱበት አፍራሽ ዓላማ ጋር የሚያያዝ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል። በመሰረቱ መታወቅ ያለበት ደግሞ በህገ-መንግስት አንቀፅ 28 ንዑስ አንቅፅ 5 ላይ እንደተደነገገው መንግስት  የህዝብን ደህንነት፣ ሰላምን፣ ጤንነትን፣ ትምህርትን፣ የህዝብን የሞራል ሁኔታ፣ የሌሎች ዜጐችን መሠረታዊ መብቶች እና ነፃነቶችን ለማረጋገጥ የሃይማኖትንና እምነትን የመግለፅ መብትን ሊገድብ ይችላል፡፡

የሃይማኖት አክራሪዎችና ፅንፈኞች ሆን ብለው ወደ ግጭትና ብጥብጥ የሚያመሩ የተለያዩ ቅስቀሣዎችን ይጠቀማሉ። ለምሣሌ አንዱን ሃይማኖት መጤ ሌላውን ነባር አድርጐ መመልከት፣ ሃገሪቱን የአንድ ሃይማኖት ተከታታይ ሀገር አድርጐ ማቅረብ፣ የአንድ ሃይማኖት ተከታዮችን የሌላው ሃይማኖት ተከታዮች ጠላት አድርጐ ማቅረብና መንግስትን ከሃይማኖት ገለልተኛ አድርጐ አለማቅረብ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህ የቅስቀሣ አስተምህሮዎች ሀገራችን ያረጋገጠችውን የእምነት ነፃነትን የሚቃረኑና በሀገራችን በሃይማኖቶች መካከል የነበረውን የሰላም፣ የመቻቻል እና የመከባበር ታሪክና ባህል ለመናድ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው። መዳረሻውም አመፅና በግዳጅ እምነታቸውን በዜጎችና በመንግስት ላይ መጫን መሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ መንግስትም ይህንን ጉዳይ መከታተል አለበት።

ሀገራችን ከነበረው የተዛባና የተሣሣተ ታሪካዊ ሂደት በተለየ አኳኋን በአሁኑ ጊዜ ዴሞክራሲን፣ ልማትንና ሰላምን ለማስፈን በታላቅ የለውጥና የህዳሴ እንቅስቃሴ ውስጥ ትገኛለች። የዴሞክራሲና የልማት አቅጣጫን በመቀየስ በአንድ በኩል የህዝቦችን የእምነት ነፃነትና ብዙህነት በማስከበር በሌላ በኩል ደግሞ የህዝባችንን የእምነት ነፃነትና ብዙህነት በማክበር ለዴሞክራሲያችን ማበብና ለልማታችን መቀላጠፍ አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታ ፈጥረን አመቻችቷል ማለት ይቻላል።፡፡ ኢትዮጵያ ሃይማኖቶችን በሚመለከት የሚትከተላቸው የሃይማኖት እኩልነት፣ የእምነት ነፃነትና

የመንግስትና ሃይማኖቶች መለያየት መርሆች ተነጣጥለው የማይሄዱና ተዳምረው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እና የዜጐችን መብቶችና ነፃነቶች የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ በዴሞክራሲና በሃይማኖት መካከል አንዳችም ዓይነት ቅራኔ ሣይፈጠር የመቻቻልና የመደጋገፍ ሁኔታ ተፈጥሮ ይገኛል።

ልማት ሰው በምድር ላይ እያለ ኑሮውን ስለሚሻሻልበት ጉዳይ የሚያተኩር ሲሆን ሃይማኖት ደግሞ ሰው ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ በኋላ ዘላቂ ፅድቅ ስለሚገኝበት ጉዳይ የሚያተኩር ነው ።ሁሉም ሃይማኖቶችና እምነቶች ከልማት ርብርቦች ጋር አብረው የሚራመዱ መሠረታዊ መርሆዎችን ያስቀምጣሉ፡፡ መርሆቹም በሥራና በራስ ውጤት ልክ ተጠቃሚ መሆን ናቸው፡፡ የሆነ ሆኖ ግን ሰርተህ ብላ የሚለውን የሃይማኖት መመሪያ  መስራት ያልቻሉትን ብቻ ለመደገፍ የተቀመጠውን መመሪያ በመጣስ ሣይሰሩ መኖርና መከበር የሚፈልጉ የተለያዩ የእምነት መሪዎችና ተከታዮቻቸው መኖራቸው አልቀረም፡፡ በተመሣሣይ መልኩ ሃይማኖትን የጥቅም ማስገኛ መሣሪያ በማድረግ የተወሰኑ አመለካከቶችን በማራመድ ከተለያዩ የውጭና የውስጥ ሃይሎች ጥቅም ለማግኘት የሚራወጡ ሰዎችም አሉ፡፡ የህዝንና መንግስት መሬትን በሃይማኖት ሽፋን በህጋዊና ህገወጥ መንገድ እየወሰዱ ለኪራይ ሰብሣቢነት መጠቀሚያ በማድረግ ህዝብን ለግጭትና ለብጥብጥ የሚያነሳሱ አካላትም እየተስተዋል ነው። ሃይማኖታዊ እምነትን ለገበያ አቅርቦ መጠቀምን የሚመርጡ ግለሰቦችና ቡድኖችም ይታያሉ፡፡ እነዚህ አድራጎቶች ከሃይማኖታዊ ስነ ምግባር ያፈነገጡ ናቸው። መንግስትም የማይደግፋቸው ናቸው።

የሃይማኖት አክራሪነትን የሃይማኖት አባቶች የቅዱሳን መፅሐፍት መሠረታዊ መርሆችን የሚፃረር እንደሆነ በማስረዳት ያወግዛሉ፡፡ መንግስት ደግሞ የሃይማኖት አክራሪነት ተግባርን የሚያየው አንዱን ወይም ሌላውን ሃይማኖት ለመራመድ መነሻ ሳይሆን ሁሉንም ዜጐች በሰላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ ዙሪያ ለማንቀሳቀስ የተደራጀ በመሆኑ  ከሰላም፣ ከልማትና ከዴሞክራሲያዊ አጀንዳዎቹ አንፃር ካለው ተፅዕኖ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ሃይማኖት አክራሪነት ፀረ-ሰላም፣ ፀረ-ልማትና ፀረ-ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ሆኖ ይገኛል፡፡ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓታችን ሁሉም ዜጐች የእምነት ነፃነት እንዳላቸው ያስቀምጣል፡፡ ዜጐች የራሣቸውን የእምነት ነፃነት ማስከበር ይችሉ ዘንድ የሌላውንም ነፃነት ማክበር እንዳለባቸው ተሰምሯል፡፡ አክራሪነት ግን የሌላውን የእምነት ነፃነት በመድፈቅና በማፈን የራስን በሌላው ላይ በሃይል የመጫን ተግባር ስለሆነ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ተግባር ነው፡፡ ይህ የአክራሪነት አመለካከት በሁሉም የሃይማኖት ተቋማት ሊታይ የሚችልና አልፎ አልፎም በተግባር የሚከሰት ነው፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ሙስሊሞች ሌላውን ቀርቶ የተለየ አመለካከት ያላቸውን ሙስሊሞች እንኳ ሣይቀሩ ሃቀኛ ሙስሊሞች አይደሉም ብለው በመፈረጅ የእምነት ተቋሞቻቸውን ለማፍረስና መቃብሮቻቸውን ቆፍረው ለማውደም ይከጅላቸዋል፡፡ ሌሎች ሃይማኖቶችም ተመሣሣይ አዝማሚያ ሊታይባቸው ይችላል፡፡ በመሆኑም ይህ አመለካከት

በሃይማኖት ሽፋን የሚካሄድ ፀረ-ዴሞክራሲ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ብጥብጥንም በመፍጠር የሚንቀሳቀስ ስለሆነም ፀረ-ሰላም አመለካከትና ተግባር ነው።

የሀገራችንን ህዝብ ለአክራሪነት አመለካከት ተጋላጭ የሚያደረገው ድህነትና ኋላቀርነት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ አክራሪዎችም በእነዚህ የህዝብ ችግሮች ላይ በመመርኮዝና ችግሮቹን በመጠቀም ነው የሚንቀሳቀሱት ፡፡

በእርግጥ ሀገራችን አክራሪነትን ለመቋቋም ትልቅ ታሪካዊና ባህላዊ አቅም አላት። የኢትዮጵያ ህዝቦች የሚያኮራና ከብዙዎቹ መሰል አገሮች የተለየ የሃይማኖት መከባበርና መቻቻል እምነትና ባህል ያላቸው ህዝቦች ናቸው።

አሁንም የአገራችን ህዝቦች የቆዩ እሴቶች የሆኑትን የመከባበር፣ የመረዳዳትና የመቻቻል ባህሎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ፤ በሃይማኖት ሽፋን የሚደረገውን ፀረ-ልማት፣ ፀረ-ዴሞክራሲና ፀረ-ሰላም የሆነውን የአክራሪነት አመለካከትና ተግባራት ጠንቅቆ በመረዳት በንቃትና በተባበረ ክንድ ማምከን ከሁሉም ዜጋ ይጠበቃል።

ቸር ሰንብቱ